የወ/መ/ቁጥር 159228

የልደታ ምድብ 1 ኛ ወንጀል ችሎት

ሐምሌ 07 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኛ ውበቱ አሰፋ

ከሳሽ፣ የፌደራል ዐ/ሕግ - አቶ መሳይ ተድላ ቀረበ

ተከሳሽ፣ አቶ ፍቅረማርያም ታደሰ እንዳለ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጠ።

<u>ፍርድ</u>

ዐ/ሕግ ጥቅምት 18 ቀን 2002 ዓ.ም በተሻፈ የወንጀል ክስ አቤቱታ ተከሳሽ በአንደኛው ክስ በ 1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 580 ላይ የተደነገገውን በመተላለፍ በሌላ ሰው ላይ ፍርሀትን ወይም ድንጋጤን በሚቀሰቅስ ሁኔታ ሐምሌ 09 ቀን 2001 ዓ.ም ከቀኑ 9፡00 ሰዓት ሲሆን በልደታ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 05/08 ክልል ልዩ ቦታው ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጊቢ ውስጥ የግል ተበዳይ አቶ ቢተው ዳዊትን አንተን አገድልሀለሁ ብሎ በመናገሩ በፈፀመው የዛቻ ወንጀል ተከሷል፤ በሁለተኛው ክስ ደግሞ በ 1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 615 ላይ የተደነገገውን በመተላለፍ በቀጥታ በመናገር ከላይ በአንደኛው ክስ በተጠቀሰው ቀን፤ ሰዓትና ቦታ የግል ተበዳይ አቶ ቢተው ዳዊትን አንተ ቆማጣ ብሎ በመናገሩ በፈፀመው የስድብና ማዋረድ ወንጀል፤ በሦስተኛው ክስ ደግሞ ተከሳሽ በ 1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 613(2) ላይ የተደነገገውን በመተላለፍ የሌላ ሰውን ክብር ወይም መልም ስም ለመጉዳት በማሰብ ከላይ በአንደኛው ክስ በተጠቀሰው ቀን፤ ሰዓትና ቦታ የግል ተበዳይ አቶ ቢተው ዳዊትን በአካባቢው ለነበሩ ሰዎች ወደ ተበዳይ እየጠቆመ ይሄ ሌባ ነው፤ አትጠጉት ብሎ በመናገሩ በፈፀመው የሀሰት ሐሜትና የስም ማጥፋት ወንጀል ተከሷል በማለት ያቀረበ ሲሆን የዐ/ሕግ የክስ አቤቱታ ለተከሳሽ ደርሶትና ተነቦለት ከተረዳው በኋላ ክሱን ሳይቃወም፤ ድርጊቱን አልፈፀምኩም፤ ጥፋተኛም አይደለሁም ብሎ ክዶ በመከራከሩ ዐ/ሕግ የግል ተበዳይን ጨምሮ ሁለት ምስክሮችን አቅርቦ ያሰማ ሲሆን እነዚህ ሁለት ምስክሮችም በደንቡ መሰረት መኃላ ፈፅመው የመሰከሩ ሲሆን በሰጡት ምስክርነትም በወቅቱ ማለትም በክሱ ላይ በተገለፀው ቀን፤ ሰዓት በዚህ በፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ግቢ ውስጥ ተከሳሽ በግል ተበዳይ ላይ የዛቻ እንዲሁም የስድብና ማዋረድ ድርጊት የፈፀመ መሆኑን ያስረዱ ስለሆነ፤ እነዚህ የተከሳሽ ድርጊቶች ደግሞ በሕግ ክልከላ የተደረገባቸው በመሆኑና ተከሳሽ ይህን የተላለፉ ስለሆነ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 580 እና 615 ስር እንዲከላከሉ ተብለው ተነግሯቸው በሁለት ቀጠሮ የመከላከያ ማስረጃ ባለማቅረባቸውና ከዚያም በላይ ለመጨረሻ ጊዜ የመከላከያ ምስክር ያቅርቡ ተብለው በታዘዙበት ጊዜ ምስክር ማቅረብ ቀርቦ መጥሪያም ወጪ ያላደረጉ በመሆኑ የተከሳሽን የመከላከያ ማስረጃ የማቅረብ መብት ፍ/ቤቱ አልፎባቸዋል። ከዚህ ለመገንዘብ የሚቻለው ደግሞ ተከሳሽ በዐ/ሕግ በኩል የቀረበባቸውን ክስና ማስረጃ

የመከላከያ ማስረጃ በማቅረብ ለማስተባበል የማይችሉ መሆኑን ነው። በመሆኑም ተከሳሽ እንዲከላከሉ በተባሉበት በወንጀል ሕግ አንቀፅ 580፤ 615 እና 613(2) ስር ጥፋተኛ ናቸው በማለት በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 149(1) መሰረት ውሳኔ ተሰጥቷል።

<u>የቅጣት አስተያየት</u>

<u>ዐ/ሕግ</u>፡ በዚህ ሐምሌ 09 ቀን 2001 የተፈፀመው የወንጀል ድርጊት በተመለከተ የምናቀርበው አስተያየት በወንጀል ሕግ አንቀፅ 84(1)(ሠ) መሰረት በአካል ጉዳተኛ በሆነ ተበዳይ ላይ የተፈፀመ ስለሆነ ቅጣቱ እንዲከብድ፤ እንዲሁም ተከሳሽ ከአንድ በላይ በሆነ ድርጊት ጥፋተኛ የተባለ ስለሆነ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 85 መሰረት ከብዶ ይወሰን፤ በተጨማሪም በወንጀል ሕግ አንቀፅ 84(1) (ሐ) መሰረት ቅጣቱ ከብዶ እንዲወሰን ምክንያቱም ተከሳሽ ሰኔ 03 ቀን 2001 ዓ.ም የወንጀል ድርጊት ፈፅሞ ጥፋተኛ የተባለና አሁን ደግሞ በድጋሜ ጥፋተኛ ስለተባለ ነው በማለት አመለከተ።

<u>ተከሳሽ</u>፡ ዕድሜዬ 34 ዓመት ነው፤ የትምህርት ደረጃዬ ዲፕሎማ ነው፤ ትደርና ልጅ የለኝም፤ የምረዳቸው እህትና ወንድሞች እንዲሁም ደካማ አባት አለኝ እነሱን እረዳለሁ፤ የወር ገቢዬ ብር 1990.00(አንድ ሺህ ዘጠኝ መቶ ዘጠና ብር) ነው፤ አሁን የምሰራው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ውስጥ በሂሳብ ሹምነት ነው፤ ድርጊቱ ተፈፀሚል ከተባለ ተከሳሽና የግል ተበዳይ የቦታ ክርክርን መሰረት አድርጎ በርካታ ክሶች ያሉን ሲሆን፤ የግል ተበዳይ በተከሳሽ ይዞታ ውስጥ እየኖሩ በፍ/ቤት ተከሰው ተፈርዶባቸው ጉዳዩ በአፈፃፀም ደረጃ ላይ ይገኛል፤ ተከሳሽ በስራ ክርክር ምክንያት ሲከራከሩ ቆይተው ተፈርዶላቸው አሁን ገና ነው ሥራ የጀመሩት፤ የመ/ቤታቸውን የሰራተኞች ደመወዝ ለማሻሻል በመስራት ላይ ናቸው፤ በመሆኑም ቅጣቱ በገንዘብ እንዲሆንልኝ፤ ይህ ካልሆነ ቅጣቱ እንዲገደብልን በማለት ከጠበቃቸው ጋር በመሆን አመልክተዋል።

ፍ/ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የሚከተለውን ቅጣት ወስኗል።

<u>ውሳኔ</u>

በወንጀል አድራጊ ላይ የሚወሰነው ቅጣት ወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ በሚያሳካ መልኩ ሊሆን እንደሚገባ የታመነ ነው። በዚህም መሰረት የወንጀል ሕግ ዓላማ ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የአገሪቱን መንግስት፤ የነዋሪዎቿን ሰላም፤ ደህንነት፤ ሥርዓት፤ መብትና ጥቅም መጠበቅና ማረጋገጥ ነው።

የወንጀል ሕግ ግብ ደግሞ በዋናነት ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ሲሆን፤ ሕጉን ተላልፈው ወንጀል የሚፈፅሙትን ደግሞ ተቀጥተው ሌሎች ወንጀል እንዳይፈፅሙ፤ እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ እርምጃዎች እንዲወሰድባቸው ማድረግ ስለመሆኑ በ 1996 ዓ.ም ከወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.የወንጀል ሕግ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል።

የወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ ለማሳካት ፍ/ቤቱ በወንጀለኛው ላይ የሚወሰነው ቅጣት በአንድ በኩል ወጥነትን፤ ተመዛዛኝነትን እና ፍትሀዊነትን ለማረጋገጥ በሌላ በኩል ደግሞ የወንጀል አድራጊውን ግላዊ ባህሪና የወንጀል አፈፃፀም ክብደት መዝኖ ቅጣት ለመወሰን እንዲያስችል ታስቦ የወጣውን የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 እና የወንጀል ሕጉን ድንጋጌዎች መሰረት ተደርጎ የሚከተለው ቅጣት ተወስኗል።

ተከሳሽ አሁን ጥፋተኛ የተባለበት በ 1996 ዓ.ም የወጣው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 615/የስድብና ማዋረድ ወንጀል፤ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 580/የዛቻ ወንጀል እና የወንጀል ሕግ አንቀፅ 613(2)/የሀሰት ሐሜት ወንጀል ገና ደረጃ ያልወጣላቸው በመሆኑ የወንጀል ደረጃ እና እርከን የሚወሰነው በቅጣት አወሳሰን መመሪያው አንቀፅ 13 መሰረት ነው። የደረጃ አወሳሰኑም ማክበጃውና ማቅለያው ታሳቢ ከመደረጉ በፊት በወንጀሉ ክብደትና አፈፃፀም መሰረት እንደሚወሰን መመሪያው በደነገገው መሰረት ደረጃው በሦስት ደረጃዎች ሀ. ዝቅተኛ፤ ለ. መካከለኛ እና ሐ. ከባድ ደረጃ በማለት ይለያል።

ፍ/ቤቱም በወንጀሉ ክብደትና አፈፃፀም መሰረት የወንጀሉን ደረጃ ለመወሰን የስድብና ማዋረድ ወንጀል አፈፃፀሙ ሲታይ ተከሳሽ የተለየ ድርጊታቸውን ከባድ የሚያደርገው ነገር ፍ/ቤቱ ስላላገኘ፤ የዛቻ ወንጀል ድርጊቱም በቀንና ሰዎች ባሉበትና ያለመሳሪያ የፈፀሙት በመሆኑ፤ በሦስተኛው የወንጀል ድርጊትም የሀሰት ሐሜት ወንጀሉ የተለየ ድርጊቱን ከባድ ነው የሚያስብል ነገር ስላልተገኘ የወንጀል ደረጃዎቹ ዝቅተኛ ናቸው ተብሎ ተወስኗል።

በወጣው ደረጃ መሰረት እርከን ለመወሰን በሕጉ አንቀፅ 615 ለወንጀሉ የተቀመጠው ቅጣት ከሦስት መቶ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከሦስት ወር በማይበልጥ ቀላል እስራት፤ ለወንጀል ሕግ አንቀፅ 580 ከአምስት መቶ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከስድስት ወር በማይበልጥ ቀላል እስራት፤ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 613(2) ላይ ለተመለከተው ደግሞ ከአንድ ወር በማያንስ ቀላል እስራት እና በመቀጮ ያስቀጣል። ከሁለቱ የቅጣት አይነቶች በቅድሚያ ፍ/ቤቱ አንዱን መለየት ስላለበት ከተፈፀመው የወንጀል ድርጊት አንፃር ተከሳሽን ያርማል፤ ወደፊትም ያስተምራል ብሎ ፍ/ቤቱ ያመነው የእስራት ቅጣትን በመሆኑ ተከሳሽ በእስራት እንዲቀጡ ተወስኗል።

ከዚህ በላይ በተመለከተው የቅጣት ደረጃ መሰረት እርከኑን ለመወሰን እያንዳንዱ የወንጀል ድንጋጌን ለአራት እኩል በማካፈል የሚመጣው ስሌት ለዛቻ ወንጀሉ ከአስር ቀን እስከ አንድ ወር ከሃያ ቀን ቀላል እስራት

ሲሆን ለስድብና ማዋረድ ወንጀሉ ከአስር ቀን እስከ ሰላሳ ቀን(ወይም አንድ ወር) ቀላል እስራት፤ ለሀሰት ሐሜት ወንጀሉ ደግሞ ከአንድ ወር እስከ ዘጠኝ ወር ነው። በዚህ መሰረት ለስድብና ማዋረድ ወንጀሉ መነሻ ቅጣቱ ሃያ(20) ቀን፤ ለዛቻ ወንጀሉ ሰላሳ ቀን(አንድ ወር)፤ ለሀሰት ሐሜት ወንጀሉ ደግሞ አራት ወር ነው። ተከሳሽ ተደራራቢ ጥፋት ስለፈፀሙ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 184(1) (ለ) መሰረት የሦስቱ ቅጣት ድምር አምስት ወር ከሃያ ቀን ሲሆን ይህ ደግሞ በአባሪ 1 መሰረት በእርከን 4 ላይ የተመለከተ ስለሆነ የእርከን 4 ደግሞ ፍቅድ ስልጣኑ ከአራት ወር እስከ ሰባት ወር ነው።

ከዚህ በመነሳት የግራቀኙን የቅጣት አስተያየት አመዛዝኖ ለመወሰን ዐ/ሕግ በተጠየቀው መሰረት በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 84(1)(ሐ) እና (ሠ) መሰረት ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት ያቀረበ ስለሆነ ፍ/ቤቱም ምክንያቶቹን እንመረመራቸው ተከሳሽ ሰኔ 03 ቀን በዚሁ በአሁን የግል ተበዳይ ላይ የስድብና ማዋረድ ወንጀል ፈፅመዋል ተብለው በመዝገብ ቁጥር 160651 ጥፋተኛ የተባሉ ስለሆነ፤ ይህ ደግሞ ደጋጋሚነትን የሚያሳይ በመሆኑ፤ እንዲሁም የግል ተበዳይ አካል ጉዳተኛ ሲሆን በዚህ ግለሰብ ላይ የወንጀል ድርጊትን መፈፀም የቅጣት ማክበጃ ስለሆነ፤ በድምሩ ዐ/ሕግ 2 ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶችን ያቀረበ ስለሆነ ፍ/ቤቱም ከላይ የተገለፀውን እርከን 4 የነበረውን መነሻ ቅጣት ወደ እርከን 6 ከፍ አድርጎታል።

ተከሳሽም የቅጣት አስተያየት እንዲያቀርቡ ተጠይቀው በወንጀል ሕግ አንቀፅ 82 እና 86 መሰረት በማስረጃ የተደገፈ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ያላቀረቡ በመሆኑ የቅጣቱን እርከን ፍ/ቤቱ ዝቅ አላደረውም።

ስለሆነም ከላይ እንደተገለፀው ቅጣቱ በአባሪ አንድ እርከን 6 ላይ የተመለከተው ፍቅድ ስልጣን/range/ ከስምንት ወር እስከ አንድ ዓመት ቀላል እስራት የሚያስቀጣ ሲሆን ፍ/ቤቱም ተከሳሽን በአስር ወር ቀላል እስራት፤ እንዲቀጡ ወስኗል።

በወንጀል ሕግ አንቀፅ 613(2) ላይ የተመለከተው ጥፋት የእስራት ቅጣት መቀጫ ብቻ ሳይሆን የገንዘብ መቀጮ ጭምር ያለው ስለሆነ፤ የወንጀሉ ደረጃ ዝቅተኛ ተብሎ የተመደበ ስለሆነ፤ በቅጣት አወሳሰን መመሪያው አንቀፅ 13(10) መሰረት ለዝቅተኛ የወንጀል ደረጃው ቅጣቱ የሚወሰነው በብር 10 እና 3300 መካከል ስለሆነ ከተከሳሽ ገቢ አንፃር ብር 600.00(ስደስት መቶ ብር) እንዲቀጡ ተወስኗል።

<u>ትዕዛዝ</u>

1 ኛ. በተከሳሽ ላይ የተወሰነውን የእስራት ቅጣት የአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት እንዲያስፈፅም ታዟል። ይፃፍ።

2 ኛ. በዚህ መዝገብ የተገባ የዋስትና ግዴታ ቀሪ ሆኗል።

3 ኛ. የይግባኝ መብት እንዳለ በችሎት ተነገረ።

4 ኛ. መዝገቡ ተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።